



ትምህርት 11 ለ ሰኔ
6፣ 2018

# መሰናክሎች







“ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን
እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን
እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን፤
በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር
በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።”
(ሮሜ 5:3-5)





የምንኖረው ኃጥያትና መከራ በበዛበት ዓለም ውስጥ ነው። የሆነ ወቅት ላይ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ፍቅር እንድንጠራጠር የሚያደርጉን ሁኔታዎችን መጋፈጣችን የማይቀር ነው።

ለእነዚህ መሰናክሎች ምላሽ የምንሰጠው እንዴት ነው?

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባህሪያት በልዩ ልዩ አስከፊ ሁኔታዎች ውስጥ ሲያልፉ የሰጡትን ምላሽ በማጥናት እኛም በተመሳሳይ አጣብቂኞች ውስጥ ስንገባ የእነርሱን ምሳሌ ተከትለን እንዴት እንደምናልፍ እንመለከታለን።

**የህይወት ማዕበሎች**



**በሽታዎች**



**ቀውስ**




**ሃዘን**



**ኢየሱስን ማየት**





# የህይወት ማዕበሎች

“ብርቱ ዐውሎ ነፋስም ተነሣና ውኃ በታንኳይቱ እስኪሞላ ድረስ ማዕበሉ በታንኳይቱ ይገባ ነበር።”
(ማርቆስ 4:37)



በሌሊት የገሊላን ባህር ማቋረጥ በማዕበልም ውስጥ እንኳን ቢሆን የተካኑ አሳ አጥማጆች ለነበሩት ለጴጥሮስ፣ ለእንድርያስ፣ ለያዕቆብና ለዮሐንስ አዲስ ነገር አልነበረም።

ነገር ግን ማዕበሉ ከአቅማቸው በላይ ነበር። አውሎ ነፋሱ ማዕበሉን ሲያስነሳው መርከቢቱን በውሃ ሞላትና ህይወታቸውን በአደጋ ላይ ጣለው። ያን ጊዜ “ኢየሱስ በየት ነው?” ብለው ጮኹ። ተኝቶ ነው ያለው? የማይረዳን ለምንድን ነው? እኛ ላይ ስለሚሆነው ግድ አይለውምን? (ማር 4:35-38)



በህይወታችን በማዕበሎች ውስጥ እናልፋለን። ኢየሱስን እርዳታ እንጠይቀዋለን ነገር ግን የተኛ ይመስል ዝም ይለናል። መገኘቱም አይሰማንም። ነገር ግን እርሱ አብሮን አለ።

ማዕበሉን “ዝም በል፥ ፀጥ በል” ብሎ እስኪገስጸው ድረስ እንጠብቀው (ማር 4:39)። እርሱ ስለኛ ግድ ይለዋል (1 ጴጥ 5:7)። የተነሳብንን ማዕበል ጸጥ ያደርግልናል። ታዲያ ያን ጊዜ ማመስገንን አንርሳ (ማር 4:40-41)።




# በሽታዎች

“ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደ ሆነ እድናለሁ ብላለችና።”
(ማርቆስ 5:28)



አስራ ሁለት ዓመት ደም እየፈሰሳት ስትሰቃይ የነበረች አንዷት ሴት ፈውስን የሚሰጣት አንድም ሃኪም ባለመኖሩ ንብረቷን ጨርሳና ተስፋ ቆርጣ ነበር (ማር 5:25-26)። ዛሬም አንዳንድ አገራት ነፃ የህክምና አገልግሎት ቢኖራቸውም በተቀረው ዓለም ግን እንደዚሁ የሚሰቃዩ ሰዎች አሉ።



ለማንኛውም ግን ሁላችንም ህመም በሰቆቃ አስሮና አስጨንቆን የምናልፍበትን ሁኔታ እንጋፈጣለን።

ሴቲቱ በኢየሱስ ዘንድ መድኃኒቷን አይታለች፤ እምነቷም አዳናት (ማር 5:27-29)።

ኢየሱስ የተካኑ ሀኪሞችን ተጠቅሞ ሊፈውሰን ወይም ደግሞ በቀጥታ በተዓምሩ ሊያድነን ይቻለዋል።





ኢየሱስ ሸክማችንንና ጭንቀታችንን በእርሱ ላይ እንድንተወው ዛሬም ይጠራናል (ማቴ 11:28-30)።

# ቀውስ

“ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ፥
በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ።” (ኢዮብ 19:26)



ጦርነት፣ ጠላት እና የተፈጥሮ አደጋዎች የኢዮብን ህይወት እንዳልነበረ አደረጉት (ኢዮብ 1:13-19)። በተፈጥሮ ወይም በዚህ ዓለም ላይ በሚሰራው ክፉ ምክንያት ሁላችንም ለህመም ተጋላጮች ነን።

ምላሻችን ምን ይሆን? ኢዮብ ምላሽ የሰጠው እንዴት ነበር?



- እግዚአብሔርን አልወቀሰውም አልተወውምም
- በሙሉ ኃይሉ እግዚአብሔርን ተጠማጠመ
- በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ እንኳን እግዚአብሔርን ታመነ
- ክብር የተሞላበት የወደፊት እጣ ፈንታውን ትኩር ብሎ ተመለከተ (ኢዮብ 19:25-27)

ተስፋ ባንቆርጥ እጅግ ከባድ በሆኑ ፈተናዎች ውስጥ ስናልፍ እንኳን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሆነ ማስተዋል እንችላለን። እርሱ ይወደናል እናም ከድካም ውስጥ ብርታትን፣ ከተስፋ መቁረጥ ውስጥ ጽናትን፣ ከችግር ደግሞ ተስፋን እንድናወጣ ያነሳሳናል (ኢዮኤል 3:10፣ ሮሜ 5:3-5)።

በከባድ ጊዜያት ውስጥ እያለፋችሁ ከሆነ እግዚአብሔር ለእናንተ ያለው ፍቅር እና ጥንቃቄ በህይወታችሁ ውስጥ የማይለወጥ ነገር እንደሆነ አስታውሱ።

# ሀዘን

“እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደ ሆነ ተስፋ አድርገን ነበር፤…” (ሉቃስ 24:21a)








ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ እስራኤልን የሚቤዥ መሢህ ነው ብለው ተስፋ ቢያደርጉትም እርሱ ግን ሲሞት መራር የሆነውን እውነታ መጋፈጥ ነበረባቸው (ሉቃ 24:18-21)።

ሀዘናቸው እጅግ ታላቅ ስለነበር ኢየሱስ ከሞት መነሳቱን በአይናቸው እያዩ እንኳን ማመን ተስኖአቸው ነበር (ሉቃ 24:22-24)።

ኢየሱስ በትዕግስት ችሏቸው ተስፋቸው ተመልሶ እንዲያብብ አደረገ። በመጨረሻም “ዓይናቸውም ተከፈተ” (ሉቃ 24:31)፤ በሀዘን ውስጥ ያሉትን ሌሎቹን ደግሞ ለማጽናናት እሮጡ (ሉቃ 24:32–35፣ 2 ቆሮ 1:4)። እኛ ከእነርሱ ልምድ ምን ልንማር እንችላለን?







- ጥርጣሬ በአሳባችን ውስጥ ስር እንዲሰድድ መፍቀድ የለብንም
- ኢየሱስ በሀዘናችን ውስጥም ቢሆን አብሮን ይራመዳል
- ከፈቀድንለት ግራ መጋባታችንን ሁሉ ያነሳልናል
- ኢየሱስ ያለንበትን ሁኔታ ከእኛ በላይ ይረዳል

# ኢየሱስን ማየት

"ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።" (ሮሜ 8:18)

ኤለን ጎዋይት በመረረ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆና ሳለች ኢየሱስን በራዕይ ተመለከተችው።

ኢየሱስ እርሷ የምታልፍበትን ሁሉ እንደሚረዳት አስተዋለች። እጁንም በራሷ ላይ ጭኖ "አትፍሪ" አላት።



አስደናቂ ትዕይንቶችን ተመለከተች እናም የሰማይ ቤትን ደህንነትና ሰላም ያገኘች ያህል ተሰማት።

ይህ ህልም ተስፋንና እምነትን ሰጣት፤ እግዚአብሔርንም በመተማመን ልቧ ጸና።

"እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።" (ሮሜ 8:28)

"ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።" (ፊልጵስዩስ 4:6-7)

"ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም። [...] በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።" (ያዕቆብ 1:2-4, 12)



"እርሱም፦ ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ። እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ።" (2 ቆሮንቶስ 12:9)

"በሁሉም ሰው ጉዞ ውስጥ የጥልቅ ሀዘንና ፍጹም ተስፋ የመቁረጥ ጊዜያቶች—መሪር ሀዘን እድል ፈንታ የሆኑበት ቀናት እና እግዚአብሔር ለምድራዊ ልጆቹ መልካም አሳቢ መሆኑን ለማመን የሚያስቸግርባቸው ቀናቶች ይመጣሉ፤ በእነዚያ ቀናት ችግሮች ነፍስን ሲያስጨንቋት ሞት ከህይወት ይልቅ ተመራጭ መስሎ ሊታይ ይችላል። ብዙዎች እግዚአብሔርን መጠማጠም ትተው ለጥርጣሬ ባርነትና ለአለማመን ግዞት የሚሰጡት ይህን ጊዜ ነው። በእንዲህ አይነቶቹ ጊዜያት ላይ በመንፈሳዊ እይታ የእግዚአብሔርን እንክብካቤ ማስተዋል ብንችል መላዕክት ከራሳችን ሊያድኑን ሲሹ፣ እግሮቻችንንም ከዘላለም ተራሮች በላይ በጸናው መሠረት ሊተክሉ ሲጥሩ እንመለከታለን፤ ከዚያም አዲስ እምነትና አዲስ ህይወት ወደ ሕያውነት ይፈልቃሉ።"

EGW (ነቢያት እና ነገሥታት,ገጽ 163)